# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።
# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ“ኢትዮጵያ” የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ።

---

መጋቢት ፳፯ ቀን፥ ፲፱፻፺፮ ዓ. ም.

ይድረስ፡- ለወ/ ማክዳ ዮሐንስ፤
የማስታወቂያ ማስፋፊያና የደንበኞች አገልግሎት ዋና ክፍል ኃላፊ፤
ETHIOPIAN AIRLINES, P. O. BOX 1755, ADDIS ABEBA, ETHIOPIA
TEL: [251.1] 612 222 FAX: [251.1] 611 474 WWW. ETHIOPIANAIRLINES.COM

በእግዚአብሔር ስም፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን አቀርብልዎታለሁ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ፡ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ሲታወቅበት የኖረውን የአንበሳ ምሥል፡ በወፍ ላባ ለመለወጥ ማቀዱን፡ ከኀዋ ማስታወቂያችሁ ስለተረዳሁ፡ ምክንያቱን እንዲገልጽልኝ፡ ለሕዝብ ግንኙነት ክፍላችሁ፡ ላቀረብሁት ጥያቄ፡ ምላሽ በማጣቴ፡ ለዋናው ሥራ አስኪያጃ፡ በጥቅምት ፲፯ ቀን፥ ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. በቀጥታ መጻፌ ይታወሳል። ለዚያ ደብዳቤዬ፡ መልስ ይኾን ዘንድ፡ እርስዎ፡ መሥሪያ ቤትዎን በመወከል፡ በ“ጥር 19 ቀን፥ 1996 ዓ. ም.” የላኩልኝ መልስ፡ ከጋዜጣ መግለጫዎ በቀር፡ ከኹለት ገጾች ብርሃናውያን ሥዕሎች ጋር፡ ዘንድሮም፡ ለአገልግሎት መጥቼ በምገኝበት፡ በአሜሪካ አገር እያለሁ፡ በመጋቢት ፲፮ ቀን፥ ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. ደረሰኝ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

ከዚህ፡ የመልስ ደብዳቤዎ፡ ጠብቄው የነበረው፡ ስለምልክቱ መለወጥ፡ የሚገልጹልኝ ምክንያት፡ “አጥጋቢ ይኾናል!” የሚል ነበር። ነገር ግን፡ እንደዚያ ሳይኾን፡ እንዲያውም፡ በቀደመው ደብዳቤዬ ውስጥ የዘረዘርኋቸውን ትችቶችና አስተያየቶች፡ በበለጠ የሚያጸናና የሚያጠናክር ኾኖ ስላገኘሁት፡ ይኸው መልስዎ፡ የተፈጸመውን የጥፋት ድርጊት ለማጽደቅ፡ “ትክክልና በቂ ነው!” ብዬ ልቀበለው ያዳገተኝ መኾኔን ስገልጽልዎ፡ በኀዘኔታ ነው። ከዚህ የመልስ ደብዳቤዎ፡ የተገነዘብሁትን፡ እኔም፡ እንደርስዎ፡ ባጭር ላስረዳዎ እሞክራለሁ።

፩ኛ፡ ገና የመጀመሪያውን ገጽ ስመለከት፡ አየር መንገዱ፡ በደብዳቤ ዓርማው ላይ ሳይቀር፡ የቀድሞ የኢትዮጵያዊነት መልኩን፡ ፈጽሞ የለወጠ መኾኑን አወቅሁ፤ ይኸውም፡ **Ethiopian** የሚለው ቃል፡ እንዲህ ባሉ፡ ታላላቅ የጎሉ ባዕዳን ፊደላት፡ ከላይ ተጽፎ፡ የኢትዮጵያ የሚለው ስም ግን፡ በትናንሽ የግእዝ ፊደላት፡ ከሥሩ ተሸጉጦ መታየቱ ነው፤ ቀጥሎም፡ ከእርሱ ዝቅ ብሎ፡ AFRICA'S LINE TO THE WORLD ከሚለው፡ በባዕዳኑ ፊደልና ቋንቋ ተጽፎ ከሚነበበው መፈክር በቀር፡ በኢትዮጵያኛ ፊደል፥ ወይም ቋንቋ የተጻፈ፡ አንዳችም ተመሳሳይ የመርህ ቃል አለመኖሩ ነው፤ በመጨረሻ፡ የደብዳቤዎ፡ የቀንና የዓመተ ምሕረት ቍጥር፥ የመሥሪያ ቤትዎ ስምና አድራሻ ጭምር፡ በሙሉ የተጻፈው፡ በባዕዳኑ ቋንቋ፥ ፊደላትና አኀዝ ብቻ መኾኑ ነው።

…፪

መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፤ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭፤ ፳-00-፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
www.ethkogserv.org

፪ኛ፡ እኛ፡ ኢትዮጵያውያን፡ የእግዚአብሔር፡ የቃል ኪዳን ሕዝብ ስለኾንን፡ ከማናቸውም ፍጡር፡ ለተደረገልን ውለታ፡ "እግዚአብሔር ይስጥልን!" እንላለን እንጂ፡ ለማንም ፍጡር፡ 'ምስጋና'ን የማናቀርብ መኾናችንን እንዲያውቁልኝ አሳስብዎ ዘንድ፡ ይፍቀዱልኝ፡፡ "ምስጋና" የምንለውም፡ "ፍጡር፡ ፈጣሪው፡ ላደረገለት ቸርነት፡ ደስ ብሎት፡ ስለውለታው፡ ለፈጣሪው የሚያቀርበው መሥዋዕት ነው፤" ስለዚህ፡ "ምስጋና የሚገባው፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው!" ብለን እናምናለን፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ እርስዎ፡ *"ላመሰግንዎ እወዳለሁ"* ሲሉ፡ ለእኔ ሳይገባኝ፡ የለገሡኝን ሙገሳ፡ እንዲያነሡልኝና አገላለጽዎን፡ ወደዚህ የእምነት አቋማችን አቃንተው እንዲያስተካክሉልኝ፡ በአክብሮት እጠይቅዎታለሁ፡፡

እንዲሁም፡ ለአየር መንገድዎ፡ ስላለኝ *"ፍቅርና የባለቤትነት ስሜት"* የገለጹት በጎ አስተያየትዎ፡ እውን ኾኖ፡ ሊቀጥል ይችል የነበረው፡ አየር መንገዱ፡ በኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ እንዲቀጥል አድርጋችሁ በኾነ ነበር፤ እንዲህ፡ በይፋ፡ ኢትዮጵያዊነቱን፡ ክዶ እንዲተው በድፍረት ከወሰናችሁበትና ውሳኔያችሁንም፡ በማንአለብኝነት፡ በተግባር ላይ ካዋላችሁት በኋላማ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ወደእውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱ እስካልተመለሰ ድረስ፡ በመካከላችን፡ ምን ዓይነት "ባለቤትነትና ወዳጅነት ይኖራል!" ብለው ያስባሉ? ያማ፡ አይኖርም፡፡

፫ኛ፡ *"የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባሳለፋቸው 58 ዓመታት የአገልግሎት ዕድሜ በዓርማው ላይ መሠረታዊ ለውጥ አላደረገም፡፡ ከዚህ በፊት በአርማነት ይጠቀምበት የነበረውን የአንበሳ ምስል፥ ባንዲራና ኢትዮጵያዊ ፊደላት አሁንም ይዞ ይገኛል"* የሚለው ቃልዎ፡ በገሃድ ከተፈጸመው ድርጊት ጋር እንደማይጣጣም፡ እንዴት ሳያስተውሉት ቀሩ!? ታዲያ፡ ለውጥ ከሌለ፡ *"ይኸው፡ አዲስ ምልክት አወጣን!"* እየተባለ፡ በየመድረኩ ላይና በብዙኃን መገናኛዎች አማካይነት፡ ያ ኹሉ የማስታወቂያ ልፈፋ ስለምን ተደረገ? ይህ በጽሑፍ ያሠፈሩት ቃልዎ፡ እውን ኾኖ፡ ተፈጻሚነትን ያገኘ ቢኾንማ ኖሮ፡ በደብዳቤዎ አርእስት ላይ፡ በግርማው፡ ጉብ ብሎ፡ እያገሣ፡ ሊታይ ይገባው የነበረው፡ የወፍ ላባው ሳይኾን፡ የአንበሳው ምሥል ብቻ ነበር፡፡ የእናንተ ውሳኔና ድርጊት ግን፡ በዚህ አንጻር፡ የዚህ እውነታ፡ ተቃራኒ የኾነው ክፉ ግብር ኾኖ ተገኘ፡፡

ደግሞም፡ ዓላማችሁ፡ በእርግጥ፡ እንዳጻጻፍዎ፡ *"ኢትዮጵያዊ መለያውን ሳይለቅ፡ ዓለም አቀፋዊነትንና ዘመናዊነትን ለማላበስ"* ቢኾን ኖሮ፡ በቀደመው ደብዳቤዬ ላይ እንዳብራራሁት፡ ከወፍ ላባ ይልቅ፡ የአንበሳ ግርማ ስለሚበልጥ፡ ምርጫችሁ፡ "አንበሳው" ሊኾን በተገባ ነበረ፡፡ የወፍ ላባማ፡ ምንጊዜም ቢኾን፡ ከበረራ መግለጫነት ስለማያልፍ፡ ከዚህ ሙያ ጋር የተያያዘ ሥራ ያለው ኹሉ፥ የዓለም አየር መንገዶች ጭምር፡ በወል የሚጠቀሙበት፡ የጋራ መታወቂያ እንጂ፡ ለአንድ አየር መንገድ፡ ብቸኛ መለዮ ምልክት ሊኾን እንደማይችል፡ እርስዎ፡ ራስዎም፡ ስለወፍ ላባና ስለበረራ ሥራ በጠቀሱት የታሪክ ጭብጥዎ አስረድተውናል፡፡

፬ኛ፡ *"የኢትዮጵያ አየር መንገድ፡ የመላ ኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ንብረት እንጂ፡ የአንድን ብሔር፥ ሃይማኖት፥ ወይም፡ የፖለቲካ ቡድን፡ ማንነትና ፍላጎት የሚያንጸባርቅ አለመኾኑን እየገለጽሁ፡"* ያሉት፡ ሌላው ቃልዎ፡ እርስዎ ሳያስቡት፥ ለእኔ ግን፡ ግንዛቤዬን ያጠናከረ፡ አንድ ደባ መኖሩን ከሠተ! ይኸውም፡ እርስዎና የኃላፊነት ባልደረቦችዎ፡ የአንበሳውን ምልክት፡ በተራ የወፍ ላባ ለመለወጥ የተነሣሣችሁበት ቊርጥ ምክንያታችሁ፡ ምን እንደኾነ ለማወቅ፥ በሥውር የምታካኺዱት፡ የፀረ ኢትዮጵያነት ግዳጅ መኖሩንም ለማጋለጥ፡ ያስቻለ፡ ጽኑ ማስረጃን፡ ግልጽ አድርጎ ማቅረቡና ማስጨበጡ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት፡ በቀደመው ደብዳቤዬ፡ በሚበቃ የተቸሁበትና ያብራራሁት ስለኾነ፡ አኹን፡ እዚህ ላይ፡ ያንኑ በመድገም፡ ጊዜን ማባከን አልፈልግም፤ እርሱኑ እንዲያጤኑት በማሳሰብ ብቻ፡ ምንም ነገር ሳልጨምርበት ትቼዋለሁ፡፡

እንግዴህ፡ በዚህና በቀደመው ደብዳቤዬ ውስጥ የጠቀስኳቸውን ጉዳዮች፡ “ጥቃቅን ነገሮች ናቸው!” ብለው እንደማይንቋቸውና እንደማያቃልሏቸው ተስፋ አደርጋለሁ። ከእነዚህም መካከል፡ ሳልጠቅሳቸው የማላልፈው፡ “ጥር ፲፱ ቀን፥ ፲፱፻፺፮ ዓ. ም.”፥ “መ.ሣ.ቁ. ፰፻፲፪”፥ “፶፰ ዓመታት” ተብለው ሊጻፉ ይገባቸው የነበሩት አኀዛት፡ ኢትዮጵያዊ መልካቸው ተለውጦ፡ “ጥር 19 ቀን 1996 ዓ.ም.”፥ “መ.ሣ.ቁ. 812”፥ “58 ዓመታት” ተብለው፥ ደግሞ፡ “ኤርምያስ” የሚለው፡ የመጠሪያ ስም፡ መልኩ ተለውጦ፡ “ኤርሚያስ”፥ “ብሔራዊ” የሚለው፡ የቃሉ መልክ ተለውጦ፡ “ብሄራዊ”፥ “ሰንደቅ ዓላማ” የሚለው ቃል፡ ኢትዮጵያዊ መልኩ ተለውጦ፡ በኢጣልያንኛው፡ “bandera”፥ እንዲሁም፡ “የሚሠራ”፥ “ሥራ”፥ “ኅብረ ቀለማት”፥ “ይጸድቅላቸዋል”፥ “ሕዝብና መንግሥት”፥ “እየገለጽሁ”፥ “ገጽታ” የሚሉት ቃላት፡ የሆሄያት መልካቸው ተለውጦ፡ “የሚሰራ”፥ “ስራ”፥ “ህብረ ቀለማት”፥ “ይፀድቅላቸዋል”፥ “ህዝብና መንግስት”፥ “እየገለፅኩ”፥ “ገፅታ” ተብለው፡ በደብዳቤዎ ውስጥ፡ አልፎው አልፎው፡ በስሕተት የተጻፉት አኀዞቻችንና ቃሎቻችን ይገኛሉ።

ባዕዳኑ፡ በየቋንቋቸው፡ በብርቱ የሚጠነቀቁበትን፡ የሆሄያትና የአኀዛት ባህላቸውን፡ ለየራሳቸው ጠብቀውና አክብረው፡ ይኸው፡ እኛ ጭምር እንድንጠብቅላቸውና እንድናከብርላቸው ሲያደርጉ፡ እኛ ግን፡ የራሳችን የኾነውን፡ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ሥርዓታችንን፡ ከቍምነገር ሳንቆጥረው፡ እንዲህ፡ ባለቤት ያጣ ኾኖ፡ የጥፋት ዘመቻ እየተካኼደበት በሚገኝበት ጊዜ፡ ይባስ ብለን፡ የጥፋቱ ዘመቻ፡ አባሪ ተባባሪ ኾነን መገኘታችን ያሳዝናል።

እስኪ፡ ራስዎ፡ የሠለጠኑትን፥ “አልሠለጠኑም” የተባሉትን አገሮች ጭምር ይመልከቷቸው? በባርነት ሲገዛ የኖረ፥ ወይም፡ የማንነት ታላቅ ክብሩን፡ በዓለማዊው ምናምንቴ ነገር ለውጦና አዋርዶ፡ የመገዛት ዝንባሌ ያለው ካልኾነ በቀር፡ እርስዎ በተሠማሩበት የሙያ ዓይነት ላይ ኾነ፡ በተለያየው፡ የሥራ ዘርፍ፡ የሚገኝ፡ የየትኛው አገርና ሕዝብ ዜጋ ነው፡ የራሱ የኾነውን ንቆና አቃልሎ፡ የባዕዱን በማስቀደም፡ ሲኩራራና ሲመጻደቅ የሚታየው? ይገኝ እንደኾነ፡ እስኪ፡ በማስረጃ አስደግፈው፡ ይግለጡልኝ?! ይህን የመሰለውን፡ የየራሳቸውን ቅርስ፡ በአገር ፍቅር ስሜት፡ አክብረው የጠበቁትን ባዕዳኑንማ፥ “የበለጸጉ ታላላቆችና የሠለጠኑ ኃያላን” የተባሉትን ብቻ ሳይኾን፡ “ታናናሾችና ያልለሙ” የተባሉትን ጭምር፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የቱን ያህል፡ እያከበራቸውና እየተሽቈጠቈጠላቸው፥ እየፈራቸውና ፈቃዳቸውን እየፈጸመላቸው፥ እየተገዛላቸውም እንዳለ፡ ይኸው፡ እየታየ አይደለምን?

ምናልባት፡ እኒህን የመሰሉትን ነገሮች፡ እንዲህ፡ ቍም ነገር አድርጌ፡ በደብዳቤ በማንሣቴ፡ ነገሮቹን ብቻ ሳይኾን፡ እኔን ጭምር፡ ያቃልሉኝ ይኾናል፤ ነገር ግን፡ አይደለም፤ “የጨው ክምር ሲናድ፡ ሞኝ፡ ይስቃል፤ ብልህ ያለቅሳል!” ደግሞም፡ ልጁ፡ በሥርቆት ልማዱ ምክንያት፡ የነፍሰ ገዳይነት ወንጀልን በመፈጸሙ፡ ተፈርዶበት፡ ለስቅላት ሲወስዱት፡ እናቱ፡ “'ወየው ልጄ! ምነው እንዲህ አደረግኸኝ?' እያለች ስታለቅስበት፡ ዘወር ብሎ፡ 'እናቴ! በዚያ ልጅነቴ፡ ገና፡ ዕንቍላል መሥረቅ ስጀምር፡ ቀጥተሽኝ በኾነ ኖሮ፡ ከዚህ ጥፋት ባልደረስሁ ነበር!?' ሲል መለሰላት” እየተባለ፡ በአገራችን፡ ከትውልድ ወደትውልድ ሲወራረስ የኖረ፡ የምሳሌ አነጋገር መኖሩን ያውቁ ይመስለኛል። ይህ፡ የዛሬው፡ የኢትዮጵያ ትውልድም፡ ይህን የመሰለውን ቅርሱን፡ አቃልሎ ስለናቀውና ስለተወው፡ ማንነቱና ክብሩ ብቻ ሳይኾን፡ ራሱ ሰብእናውም ሳይቀር፡ ይኸው፡ በዓለም ሕዝብ ፊት፡ እንዴት፡ የተናቀና የተዋረደ ኾኖ ከውድቀት እንደደረሰ፡ ራስዎ ጭምር፡ ምስክር ኾነው እንደሚያረጋግጡት አምናለሁ።

በአጠቃላይ፡ ከደብዳቤዎ የኹለንተና ገጽታ ያገኘሁት የግንዛቤ ውጤት ቢኖር፡ በዚህ፡ በአየር መንገዱ ምልክት ላይ በተፈጸመው ታላቅ በደል፡ ተመሣጥረው የተባበሩት፡ የመሥሪያ ቤትዎ ባለሥልጣኖች ኹሉ፡ “የአገር ፍቅር” ከሚባለው፡ በነጻነት ካኖረን፡ ከመልካሙ፡ የተፈጥሮና የባሕርይ ውርሳችን፡ ፈጽመው የተራቆቱ መኾናቸውን፡ እንደገና በበለጠ ለማረጋገጥ መቻሌ ነው።

ይልቁንም፡ ይኸው ድርጊት፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ቀደም ብሎ፡ በብሔራዊ ደረጃ ከፈጸማቸው፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት ሥራዎቹ፡ ተለይቶ ስለማይታይ፡ ትውልዱ፡ ይኸው፡ እየደረሰበት ያለውን የመሰለ፡ ጽኑ መከራና ሥቃይ፡ በበዳዮቹ ላይ ሊያስከትል እንደሚችል፡ እኔ፡ አሳስብ ዘንድ፥ እናንተም፡ ታስቡበት ዘንድ፡ አስፈላጊ ይኾናል። የኢትዮጵያ ትውልድ ስል፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን በማጠቃለል መኾኑን፡ እንደተረዱልኝ እገምታለሁ።

በዚህ፡ የኢትዮጵያዊነት ጉዳይ ላይ የተፈጸመውን ድርጊት፡ እኔና እኔን የመሰሉት ኢትዮጵያውያን፡ በቀላል የማንመለከተው መኾኑን፡ ከዚያኛውም ኾነ፡ ከዚህኛው ደብዳቤዎቼ፡ የተረዱትና የሚረዱት ይመስለኛል። በቀላል እንዳንመለከተው የሚያደርገንም ምክንያት፡ ሰዎች፡ ወደዱም፡ ጠሉም፥ አመኑበትም፡ አላመኑበትም፡ <u>ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የሚነካው ማናቸውም ጉዳይ፡ በእግዚአብሔር እጅ፡ በቃል ኪዳን የተያዘ ስለኾነ ነው።</u> ለዚህ እውነታ፡ እርስዎን፡ ራስዎን፡ በምሳሌነት እንድጠቅስዎ ቢፈቅዱልኝ፡ “ማክዳ” የሚለውን፡ የታላቂቱንና የገናናዪቱን፥ የስመጥሩዪቱንም ኢትዮጵያዊት ንግሥት እናታችንን ስም፡ ወላጆችዎ፡ እርስዎ፡ ገና ሕፃን ሣሉ፡ ለምን እንደሰጡዎ ያውቃሉ? እርስዎስ፡ ነፍስ ካወቁ በኋላ፡ ለምን ተቀብለውትና አጽንተውት፡ መጠሪያዎ አደረጉት? እንዲህ ከኾነ፡ እኔ ደግሞ፡ “ይህን ስያሜ፡ በስምነቱ ብቻ ሳይኾን፡ በሃይማኖትና በምግባርም ጭምር፡ ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊነት ያብቁት!” እላለሁ፤ በዚህ አባባሌ ብቻ አላቆምም፤ ነገር ግን፡ እርስዎ፡ ለዚህ ማንነትዎ በቅተው ይገኙ ዘንድ፡ ከልቤ እንድመኝልዎ፥ እንድጸልይልዎም፡ የእኔም ኢትዮጵያዊነቴ የሚያስገድደኝ መኾኑን፡ ላመለክትዎ እወድዳለሁ።

ጽሑፌን ከመዝጋቴ በፊት፡ በቀደመውም ኾነ በዚህኛው ደብዳቤዬ ውስጥ ስለተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች፡ በበለጠ ለመረዳት፡ በእርግጥ የሚፈልጉ ቢኾን፡ ለአየር መንገዱ ያበረከትኋቸውን፥ ወይም፡ በየመጻሕፍት መደብሩ የሚገኙትን፡ *ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ! ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!* እና Ethiopia: The Classic Case የተባሉትን፥ በቅርቡም፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ “ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት” በሚል ርእስ፡ በሦስት ተከታታይ ጥራዞች ታትሞ የሚወጣውን፡ እነዚህን መጻሕፍቴን እንዲመለከቷቸው፡ እንደገና፡ እጋብዝዎታለሁ።

አክባሪዎ፡-

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ